Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት
ኤጀንሲ

THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN INVESTMENT
AGENCY

ቀን ____
DATE

ቁጥር ____
REF.No.

የኢትዮጵያ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር (በሚኒስትር ማዕረግ)
<u>አዲስ አበባ</u>

**ጉዳዩ፡- <u>የደንብ ቁጥር 270/2005 ማሻሻያ ደንብን እና አፈፃጸሙን ስለማሳወቅ</u>**

ለባለሃብቶች የተሻለ ማበረታቻ ለመፍቀድ እንዲቻል ደንብ ቁጥር 270/2005 ደንብ ቁጥር 312/2006 በሚል ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ/ም እንደገና ተሻሽሎ ከጸደቀ በኋላ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ወጥቷል፡፡

ስለሆነም በፌዴራል ደረጃ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ላወጡና በማምረቻ የኢንዱስትሪ የሥራ መስክ ላይ ለተሰማሩ የውጭ ባለሃብቶች (ከአገር ውስጥ ባለሃብቶች ጋር በቅንጅት የሚሰሩትን የውጭ ባለሃብቶች ጨምሮ) በደንብ ቁጥር 270/2005፣ በደንብ ቁጥር 312/2006፣ እና በቦርድ መመሪያዎችና በቦርድ ውሳኔ መሠረት የሚገባቸውን የካፒታልና ሌሎች ዕቃዎች በተፈቀደላቸው መሠረት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኩል ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት የመፍቀድ ሒደት የሚቀጥል ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል በክልል ደረጃ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ላወጡ እና በማምረቻ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 10 መሠረት ከላይ በተገለጹት ደንቦች እና መመሪያዎች ላይ በመመስረት በሚመለከተው የክልል ኢንቨስትመንት መ/ቤት በኩል በአግባቡ እየታየ ይህንን ተግባር ለመፈጸም ኃላፊነት በተሰጠውና አስቀድሞ የፊርማ ናሙና በላከ ኃላፊ/ባለሙያ አማካኝነት እየተረጋገጠ ለካፒታል ዕቃዎች የቀረጥ ነጻ ማበረታቻ ፈቃድ (ውሳኔ) ሊሰጥ እንደሚገባ ታምኖበታል፡፡

ስልክ 011- 551 00 33
Tel. 011-553 72 86
✉ 2313
Website = www. ethioinvest.org
E-mail address = ...
ፋክስ
Fax: 011-551 43 06

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

ከዚህም በተጨማሪ በግብርና ሆርቲካልቸርን (አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ዕጸ-ጣዕም ወዘተ) ጨምሮ እና በአገልግሎት የኢንቨስትመንት የሥራ ዘርፍ ላይ ለተሠማሩ የውጭም ሆነ የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ከላይ በተመለከቱት ደንቦችና መመሪያዎች ላይ በመመስረት ለውጭ ባለሃብቶች (ከአገር ውስጥ ባለሃብቶች ጋር በቅንጅት የሚሰሩትን የውጭ ባለሃብቶች ጨምሮ) በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኩል፤ እንዲሁም ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች ፈቃዱን ከሰጠው የክልል የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት በሚላክ የፕሮጀክቱ (ድርጅቱ) አፈፃፀም መግለጫ እና የድጋፍ ደብዳቤ ላይ በመመስረት በኢትዮጵያ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለሥልጣን በኩል ባግባቡ እየታየ የቀረጥ ነፃ መብት የሚያገኙ መሆኑን እየገለጽን፤ ለአፈፃፀም ይረዳ ዘንድ ሰኔ 7 ቀን 2006 ዓ/ም በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ የወጣውን ደንብ ቁጥር 312/2006 ፎቶ ኮፒ ከዚህ ደብደቤ ጋር አያይዘን እየላክን በዚሁ መሠረት እንዲፈጸም እናሳስባለን፡፡

አባሪ፡- ደንብ ቁጥር 312/2006 (1 ኮፒ)

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ

- ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ
- ለኢትዮጵያ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለሥልጣን
  <u>አዲስ አበባ</u>

- ለምክትል ዋና ዳይሬክተሮች
- ለጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ዳይሬክቶሬት

<u>የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን</u>